# ጉባኤ ኒቅያ

የመምህሩ የተፍጻሜተ ሰማዕት ጴጥሮስን ውግዘት ተላልፎ አርዮስን ከመቀበሉም በላይ፣ ሥልጣነ ክህነትን የሰጠው አኪላስ፤ በመንበረ ማርቆስ ለአንድ ዓመት ብቻ እንደቆየ መሞቱን ባለፈው አውስተናል:: እሱ ከሞተ በኋላ፣ እለ እስክንድሮስ (አሌክሳንድሮስ) (312-328) በኤጲስ ቆጶስነት ዘመኑ ለቤተ ክርስቲያን የተጋደለ የቤተ ክርስቲያን ታማኝ አባት ነው:: ዋናው የእለእስክንድሮስ ተጋድሎና ታማኝነቱ የሚነገርለት የአርዮስ ክህደት በፈነዳ ጊዜ ነው:: (በ318 ዓ.ም) በዚህ ጊዜ አርዮስ ዕድሜው የገፋ ቢኾንም፣ ከአንጾኪያ ያመጣውን አዲሱን አሳቡን በእስክንድርያ ለማስተዋወቅና ለማስመረቅ እንደ ወጣት ወጠምሻ ይሯሯጥ ነበር::

በቤተ ክርስቲያን የነጻነት ሕግ መሠረት፣ የእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን የአርዮስን የግል አስተሳሰብ ሳትቃወም ብዙ ቆይታለች:: ቤተ ክርስቲያን ብትታገሠውም፣ እሱ በድፍረት አሳቡን ለማሰራጨት፣ ለሕዝብ በሚገቡ ቃላት ሃይማኖት አዘል የኾኑ የግጥም ጽሑፎችን እያዘጋጀ፣ ለእንጨት ሰባሪዎችና ለውሀ ቀጂዎች ለነጋዴውና ላራሹ ኹሉ ያድል ጀመር፤ እንደ ዛሬው መጤ ሃይማኖቶች:: ሰውም ከስድ ንባብ ይልቅ ግጥም ማንበብ ስለሚወድና በግጥም ያነበበውም ስለማይጠፋው በዚህ እየተሳበ የአርዮስ ክህደት ሳያውቀው ገባበት:: ሃይማኖትን ለማስለወጥ የመናፍቃን ዋና መሣሪያ ግጥምና መዝሙር ማዘጋጀት ነውና:: ይህ የአርዮስ የግጥም መጣፍ ታሊያ ይባላል፤ ማዕድ ማለት ነው ይሉታል:: በዚህ የግጥም መጣፉ፣ ልብ ወለድ የፍልስፍና ቃላትና ከመጽሐፍ ቅዱስም ለራሱ አስተሳሰብ እንዲስማማ አድርጎ የተረጎማቸውን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ባያሌው አግበስብሶበት ነበር፤ ለምሳሌ ሰሎሞን 8÷22::

አርዮስ በዚህ አኳኋን ብዙ የዋሃንን ማወናበድ ስለ ጀመረ፣ የእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን የተቃውሞ ደወሏን ማሰማት ግድ ኾነባት:: ሊቀ ጳጳሱ እለ እስክንድሮስም አርዮስን ለማግባባት ብዙ ደክሞ ነበር:: ነገር ግን፣ «ያዳቆነ ሰይጣን ሳያቀስ አይለቅም» እንዲሉ፣ አርዮስ አሻፈረኝ ብሎታል:: እለ እስክንድሮስም ሙከራው ውጤት እንዳላስገኘለት ተገንዝቦ፣ በቤተ ክርስቲያን ትምህርት መሠረት (ማቴ 18÷15-16)፣ በ320 ዓ.ም፣ አርዮስ የይፋ ትምህርት ማስተማር በጀመረ በሁለት ዓመት ማለት ነው፣ አንድ መቶ የሚያህሉ የሊብያንና የእስክንድርያን ኤጲስቆጶሳት ሰብስቦ፣ የአርዮስን አስተሳሰብ ገለጸላቸው፤ ከዚህም ጋር አርዮስ ይህን ትምህርት እንዳያስተምር ነገሩም እንዳይካረርና ቤተ ክርስቲያንን እንዳያበጣብጥ፣ ብዙ ጊዜ መክሮት ያልሰማ መኾኑን ለጉባኤው አስረድቷል:: ጉባኤው የአርዮስን እንቢተኛነት ከተረዳ በኋላ ባንድ ድምጽ አወገዘው:: አሻፈረኝ፤ ከስሕተቴ አልመለስም በማለቱ ከተወገዘ በኋላ፣ ነገሩ በዚሁ እንዳያበቃና በቤተ ክርስቲያን ሰላም እንዳይመሠረት የእለ እስክንድሮስን ስም ያጠፋሁ መስሎት፣ ሊቀ ጳጳሱ የሰብአልዮስን ክህደት ያስተምራል እያለ በየደረሰበት እለእስክንድሮስን ይለፍ ጀመር:: ከዚያ ጊዜ ጀምሮ «ወልድ» የባሕርይ አምላክ ነው የሚሉ ኹሉ በአርዮሳውያን ዘንድ ሰብአልዮሳውያን እየተባሉ መጠራት ጀመሩ:: ነገር ግን የሰብአልዮስ ትምህርት ከነዚህ ትምህርት ጋር ምንም ዝምድና የለውም ማለት «ወልድ በባሕርዩ አምላክ ነው፤ ፍጡር፣ ግቡር አይደለም» ማለትና አንድ ገጽ ብሎ ማስተማር በንባብም በመንፈስም የተለያዩ ናቸው:: አርዮስ ግን ቢቸግረው አሳቡን ያልተቀበሉት ኹሉ ሰብአልዮሳውያን ናቸው ይል ነበር:: ይህ ለፈፋ በእስክንድርያ ተቀባይ ስላጣ አርዮስ ከእስክንድርያ ወጥቶ ወደ ፍልስጥኤም ምድር ሔደ:: ከዚያም ወደ ሶርያና ወደ ቂሳርያም እየዞረ በአንጾኪያ የትምህርት ቤት ጓደኞቹ ለነበሩት ኹሉ «እለእስክንድሮስ በግፍ አውግዞ አባረረኝ፤ እሱም የሰብአልዮስን ክሕደት እያስተማረ ነው፤ እንዴት የናንተ ጓደኛ ሁኜ ይህ ሁሉ ጥቃት ይድረስብኝ» እያለ ነገሩን ለሁሉም አደረሰው::

ከአርዮስ ጓደኞች አንዱ፣ በጣም የሚቀረቀርለት የኒቆሜዲያ ኤጲስ ቆጶስ አውሳብዮስ ነበር፡፤ አርዮስም ይህን ኹሉ ዘርዝሮ የጻፈለት ለሱው ነው:: አውሳብዮስ በቆስጠንጢኖስ ቤተ መንግሥት ባለሙሉ ሥልጣን ስለነበረ፣ ይህ የአርዮስ መልእክት እንደ ደረሰው ባንድ ወገበር ካንድ መምህር ከሉቅያኖስ ሲማሩ ያደጉ የሃይማኖት ወንድምአማቾች ናቸውና ወደ ኒቆሚዲያ ገሥግሦ እንዲመጣ ጥሪ አደረገለት:: ወዲያውም በአካባቢው የሚገኙ ኤጲስቆጶሳት ኹሉ አርዮስን በመደገፍ እለእስክንድሮስን እንዲያወግዙ ውስጠ ትእዛዝነት ያለው ያደራ መልእክት አስተላለፈ፤ ባለ ዘመን ነበርና «ውግዴ በዘመኑ» እንዲሉ:: ቍስጥንጥንያ እስክትመሠረት ድረስ፤ የምስራቁ ሮም ክፍል ዋና ከተማ ኒቆሜዲያ ነበረች:: አርዮስ ወደ ኒቆሜዲያ በመጣ ጊዜ፣ አውሳብዮስ አይዞህ ብሎ ተቀብሎ ከሱው ጋር አስቀመጠው:: ወዲያውም በሀገረ ስብከቱ ዙሪያ የሚገኙ ጥቂቶች ኤጲስቆጶሳትን ሰብስቦ ስለ አርዮስ ጉዳይ ሲኖዶስ አደረገ:: ሲኖዶሱን በሊቀ መንበርነት የመራው እሱው ራሱ አውሳብዮስ ነበር:: ሲኖዶሱ ስብሰባውን እንዳገባደደ፣ አርዮስም የሃይማኖቱን ምስጢርና ከእስክንድርያም በግፍ መባረሩን በሚያሳዝን ኹኔታ አብራርቶ ተናገረ:: ጉባኤውም ባንድ ሰው ብቻ የሚመራ ስለነበረ፣ ሃይማኖቱ ትክክለኛ ነውና መወገዝ አይገባውም ብሎ ፈረደለት ከላይ እንደገለጥነው አርዮስን እንዲደግፉ አደራ የተጣለባቸው ኤጲስ ቆጶሳትና ለሱም የትምህርት ቤት ጓደኞቹ እነ አውሳብዮስ ዘቂሣርያ እለእስክድሮስንና የእስክንድርያን ቤተ ክርስቲያን ሲኖዶስ በማጥላላት ለአርዮስ የድጋፍ ድምጽ አሰምተዋል::

ይህ ጉባኤ ያስተላለፈው ውሳኔ የአርዮስን ወደ ቤተ ክርስቲያን መመለስ ስለኾነ፣ አርዮስም በዚያው በእስክንድርያ እንጂ በሌላ ቦታ ለመኖር ስላልፈለገ፣ ወደ እስክንድርያ እንዲመለስ ተደረገ:: ይህ ኹሉ ሲኾን ስለ ጉባኤው መሰብሰብም ሆነ ስላስተላለፈው ውሳኔ የእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን አልሰማችም ነበር:: ስለ ኹኔታውም መጠየቅ ሲገባት አልተጠየቀችም:: ያም ኾነ ይህ አርዮስ በ322 ዓ.ም ወደ እስክንድርያ ተመለሰ:: «ወፈ ገዝት» እለእስክንድሮስ ቢያወግዘኝ ተፈትቼ መጣሁ እያለ በማንአለብኝ ያንኑ በፊት የተወገዘበት ክህደት ያስተምር ጀመር:: በዚህ ጊዜ ከፊተኛው የበለጠ በግብጽ በሊብያና በእስክንድርያ ብዙ ጆሌ አበጀ::

የክርስትና ሃይማኖት ገና በለጋው እንዳለ፣ ይልቁንም በአረማውያንና በአይሁድ መካከል በነበረችው በእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን ይህ የአርዮስ መርዝ በመነዛቱ፣ ብዙ ሰዎች ክርስቲያኖችን ወይም እምነቱን ራሱን ማፌዣ አድርገውት ነበር:: ይህ ኹኔታ እየተባባሰ መሔዱ በእስክንድርያ ብቻ ሳይሆን በቆስጠንጢኖስ ቤተ መንግሥትም ግፊትን ማሳደሩ አልቀረም:: ከዚህም የተነሣ ነገሩን በደንብ ለመረዳትና ተጨባጭ መፍትሔም እንዲገኝለት በማሰብ፣ ቆስጠንጢኖስ የመጀመሪያውን መልእክተኛ ወዳጁን የእስፓኝ ጳጳስ አስዮስን (ሆስዮስን) ወደ እስክንድርያ ላከው:: ሆስዮስም መልእክቱን አድርሶ ከእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን አባቶች ጋር ሲወያዩ ከሰነበተ በኋላ መረጃ፣ ሰብስቦ ወደ ቆስጠንጢኖስ ተመለሰ:: ስለ ተላከበት ጉዳይ ጠቡና ግዝቱ የሃይማኖት እንጂ የአስተዳደር ስላልሆነ፣ በጉባኤ መታየት አለበት ብሎ ለንጉሡ አማከረው፤ በዚህ ጊዜ ቆስጠንጢኖስ ያን ጊዜ በነበረው የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ጉባኤ እንዲደረግ አዋጅ ነገረ::

ለመጀመሪያ ጉባኤው እንዲደረግ የታሰበው በዕንቆራ (የዛሬው አንካራ) ነበር፤ በኋላ ግን ባልታወቀ ምክንያት በኒቅያ እንዲሆን ተመስኗል:: በዚህ አዋጅ መሠረት፣ የቤተ ክርስቲያን አባቶች ኤጲስቆጶሳትና ሊቃውንት በኒቅያ ተሰበሰቡ፤ ከተሰበሰቡት አባቶች አምስት ብቻ ከምዕራብ አውሮፓ የመጡ ሲኾኑ፣ የቀሩት ግን ምሥራቃውያን ናቸው:: ከነሱም የእስክንድርያው ሊቀ ጳጳስ እለእስክንድሮስና ባለቀረኝ ኹኖ አብሮት የመጣው ሊቀ ዲያቆኑ አትናቴዎስ፤ የአንጾኪያው ኤዎስጣቴዎስና የንጽቢኑ ያዕቆብ ይገኙ -ባቸዋል::

በሲኖዶሱ የተሰበሰቡት አባቶች በሕይወታቸው ንጽሕናና ቅድስና መሰል የሌላቸው፣ በሃይማኖታቸው የሐዋርያትን ፈለግ የተከተሉ ነበሩ:: ስለ ሃይማኖታቸውም በሚመሰክሩበት ጊዜ በተቃዋሚዎች በሚፈጸምባቸው የግፍ ድርጊት ዐይናቸው የፈረጠ፣ እጅ እግራቸው የተቆራረጠ ነበሩ፤ ከዚህም ኹሉ ጋር በገቢረ ተአምራት ከፍ ያለ ዝና ያላቸው ነበሩ:: ቍጥራቸውም አትናቴዎስ እንደ መሠከረው 318 ናቸው:: ሌሎች የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ጸሐፊዎች ከፍና ዝቅ አድርገው ጽፈዋል:: ለምሳሌ አውሳብዮስ የቂሣሪያው ኤጴስ ቆጶስ 250 ነበሩ ይላል:: ሌላው የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ጸሐፊ ሶቅራጥስ 300 ነበሩ ሲል፣ ሶዞሜን የተባለው ደግሞ 320 ነበሩ ብሏል:: ይሁን እንጂ ቤተ ክርስቲያን የተቀበለችው ቍጥር የመጀመሪያውን የአትናቴዎስን ነው:: «ዘዋሕድ ምስለ አብ» የሚለውን ኦርቶዶክሳዊ እምነት፣ እንደ አንድ ልብ መካሪ እንደ አንድ ቃል ተናጋሪ ኹነው ተስማምተው የተቀበሉት 318ቱ ብቻ ነበሩና::

ጉባኤው የሃይማኖት ውሳኔ የሚሰጥበት ስለ ነበር እንደ ሐዋርያት ጉባኤ የኤጲስ ቆጳሳት ብቻ አልነበረም:: ሶዞሜን የተባለው የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ጸሐፊ እንዳቀረበው የግሪክ ፈላስፎችና አርጌንሳውያን፣ የአርዮስ ደጋፊዎችም እንዳያሙ በብዛት ተጠርተው መጥተው ነበር:: ኦርቶዶክሳውያን ታዛቢዎች ግን ጥቂቶች ነበሩ:: ከኦርቶዶክሶች ወገን ኤዎስጣቴዎስ ዘአንጾኪያ አትናቴዎስ ዘእስክንድርያና ያዕቆብ ዘንጽቢን ዋነኞች ነበሩ:: ጉባኤውን በሊቀ መንበርነት እንዲመሩ የተመረጡ ሦስት ሰዎች ሲኾኑ ከነሱም ኹለቱ ሊቃነ ጳጳሳት የእስክንድርያው እለእስክንድሮስና የአንጾኪያው ኤዎስጣቴዎስ ናቸው:: ሦስተኛው ደግሞ በመጀመሪያ የንጉሡ መልክተኛ ኹኖ ወደ እስክንድርያ ሔዶ የነበረው የእስፓኝ ኤጲስ ቆጶስ ኦስዮስ ነው:: አንዳንድ ታሪክ ጸሐፊዎች የጉባኤው ሊቀ መንበር ራሱ ንጉሡ ቆስጠንቲኖስ ነበር ይላሉ::

ነገር ግን በጉባኤው መግቢያ ላይ ንግግር ካደረገ በኋላ፣ ጥቂት ተቀምጦ እንደሆነ እንጂ፣ ገና ያልተጠመቀው፣ ስለ ክርስትና ዶግማ ምንም የሚያውቀው የሌለው ንጉሥ፣ ለዚህ ታላቅ የሃይማኖት ጉባኤ ሊቀ መንበር ነበር ለማለት ያስቸግራል:: ምንም እንኳ እሱ «ንጉሥ ትሆኝ እንዳሻሽ ትሆኝ» እንዲሉ፣ መንግሥታዊ ሥልጣኑን ጋሻ አድርጎ ይህን አሳብ ሞክሮት ቢሆን ኑሮ፣ የተሰበሰቡት የቤተ ክርስቲያን አባቶች አይቀበሉትም ነበር:: ይህም ወደፊት እንደምናየው ቆስጠንጢኖስ ከአትናቴዎስ ጋር በነበረው አለመግባባት ይታወቃል:: (ቆስጠንጢኖስ የኒቂያን ጉባኤ ሊቀ መንበር ኹኖ መርቷል አርዮስ ተረታ የተባለውም በንጉሡ ተጽእኖ ነው የሚሉ የጥንት ተረፈ አርዮሳውያን የዛሬ ጆሆቫውያን ናቸው::)

በርግጥ ጉባኤው ሥራውን ለመጀመር ምልአተ ጉባኤ ባደረገበት ዕለት፣ ንጉሡ ቆስጠንጢኖስ እንኳን ደህና መጣችሁ ለማለት ወደ መሰብሰቢያው አዳራሽ ገብቶ ነበር:: በዚህ ጊዜ ከሊቃነ መናብርቱ አንዱ የአንጾኪያው ሊቀ ጳጳስ ኤዎስጣቴዎስ ንጉሡ ለክርስቲያኖች የፈቀደውን ሙሉ ነጻነት፣ ለክርስቲያኖች አንድነትና ኅብረት ያሳየውን በጎ ፈቃድ፣ አሁንም በቤተ ክርስቲያን ለተፈጠረው ውስጣዊ ችግር መፍትሔ እንዲገኝለት፣ ዓለም አቀፍ የቤተ ክርስቲያን ጉባኤ እንዲደረግ መፍቀዱን በማስመልከት የምስጋና ንግግር አደረገ:: ንጉሡም ለቀረበለት የምስጋናና የሙገሳ ንግግር አጸፋውን ሲመልስ እንዲህ አለ:: የቆስጠንጢኖስ ንግግር «ወዳጆቼ ዛሬ ከናንተ ጋር መገኘቴ ከምመኛቸው ታላላቅ ምኞቶች አንዱ ነው:: በናንተ በቅዱሳን አባቶች መካከል ለመገኘት ስላበቃኝ ከሁሉ በላይ የኾነውን ንጉሥ አመሰግነዋለሁ:: ይልቁንም የጋራ የኾነ አንድ አስታራቂ ውሳኔ ለመወሰን ባደረጋችሁት በዚህ ስብሰባ፣ እናንተን ለማስተናገድ ስላበቃኝ በተጨማሪ አመሰግነዋለሁ:: አሁንም አባቶቼን አደራ የምለው፣ በእግዚአብሔር በመድኃኒታችን ድል የተነሳው ርኩስ መንፈስ ባንዳንድ ምክንያት ደስታችንን እንዳያፈርሰውና ድፍረትን በተሞላ ርካሽ አነጋገር አምላካዊውን ሕግ እንዳያፈርሰው ነው::

«እኔም በበኩሌ» አለ ንጉሥ ቆስጠንጢኖስ፣ «ከማንኛውም የውጭ ጦርነት ይልቅ በእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚደረገው የርስ በርስ ጦርነት የከፋ ነው ብዬ እምለው በውጭ ከማደርገው ጦርነት እጅግ የመረረ ነው:: ጠላቶቼን ድል ካደረግሁ በኋላ፣ ከጦር (ከሞት) ከተረፉት አሽከሮቼና ቤተሰቦቼ ጋር ለመደሰትና እግዚአብሔርን ለማመስገን ሳስብ፣ እኔ ከምመኘውና ከማስበው የማይመሳሰል አዲስ ችግር በመካከላችሁ መፈጠሩን ስለሰማሁ፣ በነገሩ ብትወያዩበት አይከፋም በማለት ያለ ምንም መዘግዬት እንድትሰበሰቡ አደረግሁ፣ አሁንም በመሰብሰባችሁ ደስ አለኝ፤ ከስብሰባውም በሚገኘው ውጤት እንዳንድ ልብ መካሪ እንዳንድ ቃል ተናጋሪ ሁናችሁ በማያችሁ ጊዜ የበለጠ እንደምደሰት አምናለሁ:: እግዚአብሔር መርጦ የሾማችሁ እናንተ፣ ለሌላው በምታስተምሩበት ጊዜ ትምህርታችሁ የማይለያይ ሰላምን የተሞላ ይኹን ዘንድ፣ ስለዚህ የኹላችን መድኃኒትና ጌታ የእግዚአብሔር አገልጋዮች አባቶች ሆይ፣ ሰላማዊ ሕግን ለመመሥረትና መለያዬትን ለማጥፋት ዛሬ ነገ አትበሉ፤ ለዚህ አደራዬ ጥብቅ ነው::

ይህን ብታደርጉ ከኹሉ በላይ የሚሆን እግዚአብሔር ይደሰታል፤ ለኔም ከመጠን በላይ የሆነ ደስታን እንደ ለገሳችሁኝ እቆጥረዋለሁ:: እንደናንተ የእግዚአብሔር ባሪያ ቆስጠንጢኖስ» ይህን ተናግሮ ሲጨርስ ከዛሬ ጀምሮ በመላው ግዛቱ ለቤተ ክርስቲያን ዕድገት ለምእመናን አንድነት የመሰላቸሁን ታደርጉ ዘንድ ሙሉ ሥልጣን ሰጥቻችኋለሁ» ብሎ ለዚህም ምልክት ማረጋገጫ ይኾን ዘንድ የሥልጣንና የክብር ምልክት የኾኑትን የነገሠበትን ዘውዱን፣ ቀለበቱን፣ ሰይፉን አውልቆ ለጉባኤው አስረከበ:: ከዚህ በኋላ ቆስጠንጢኖስ በስብሰባው አዳራሽ አልቆየም፤ ወደ ቤተ መንግሥቱ ተመልሷል:: ጉባኤውም ከግንቦት ሃያ እስከ ሰኔ አሥራ ሦስት ቀን የመግቢያ ውይይት ካደረገ በኋላ ከሰኔ አሥራ አራት እስከ ነሐሴ ሃያ አምስት ክርክሩን ቀጥሏል:: አርዮስ የተረታው ነሐሴ ሃያ ሰባት ቀን ነው::

(በስንክሳራችን እንደ ተጻፈውና አባቶቻችንም እንደሚተርኩት ደግሞ ከሚያዝያ እስከ መስከረም ሃያ አንድ ድረስ ከያሉበት አባቶች ተሰበሰቡ:: ምልአተ ጉባኤ የተደረገበት ዕለት ስለሆነ የመስከረም ማርያም «የብዙኃን ማርያም» ትባላለች ብለው ይተርካሉ:: ከመስከረም ሃያ አንድ እስከ ኅዳር ዘጠኝ አበው ሱባኤ ገቡ:: ወዲያው በኅዳር ዘጠኝ ክርክሩ ተጀምሮ አርዮስ ተወገዘ::)

<u>*ጉባኤው መጀመሪያ የተነጋገረበት*</u>

1. አርዮስ ያቀረባቸውን ጥቅሶች መመርመር፤
2. ጥበብ የሚለውን ቃል እንዴት እንደ ተረጎመው ማየት፤
3. ወልድ በባሕርዩ ፍጡር ከሆነ፣ በመዳን ምሥጢር ላይ ስለሚደርሰው አደጋ፤
4. እግዚአብሔር ቃል ለሰው ልጆች ሲል ወዶ ያደረገውን ተዋርዶ፣ አርዮስ የባሕርይ ተወራጅነት ቢኖርበት ነው ስለ ማለቱ፤
5. ወልድ በባሕርዩ ፍጡር ሳለ፣ እንደ ሌሎች ፍጡራን በገድል በትሩፋት የአምላክነትን ክብር አገኘ ስለ ማለቱ::

በጉባኤው ላይ በነበረው ክርክር፣ አርዮስና ግብረ አበሮቹ የግሪኮችን ፍልስፍና ከመጽሐፍ ቅዱስም ለነሱ እንዲመች አድርገው የተረጐሟቸውን ለምሳሌ ምሳሌ ሰሎሞን ምዕራፍ ስምንት ቁጥር ሃያ ሁለትና የመሳሰሉት እየጠቀሱ ስለ ወልድ ፍጡርነት ለማስረዳት እሰጥ አገባ ሲሉ፣ ሌሎቹ እነ አትናቴዎስ ደግሞ ኢየሱስ ክርስቶስ መድኃኒት ነው፤ አዳኝ ነው፤ ማዳኑን ካመንህ የባሕርይ አምላክነቱንም ማመን አለብህ፤ የሚያድን እግዚአብሔር ብቻ መሆኑን መጽሐፍ ቅዱስ መስክሯልና እያሉ ክሱን ያስተባብሉ ነበር (ማቴ 1÷21፣ ኢሳ 45÷21፣ ሆሴዕ 13÷4፣ ሉቃስ 1÷47፣ 1ኛ ጢሞ 1÷1፣ ቲቶ 1÷3፣ ቲቶ 2÷10-13፣ ቲቶ 4÷7፣ ሐዋ 4÷12፣ 1ኛ ጢሞ 4÷10፣ ይሁዳ 25፣ ሉቃ 2÷11፣ ዮሐ 4÷42፣ ሉቃ 11÷20፣ ማቴ 12÷28፣ ማር 1÷19፣ ሉቃ 8÷39፣ ሉቃ 11÷20፣27):: በቅዱሳት መጻሕፍት ምስክርነት የወልድ አምላክነት ከሰው ልጆች የመዳን ምሥጢር ጋር የተያያዘ ነው:: እሱ አምላክ ካልሆነ ግን እኛም አልዳንንም ማለት ነው:: በሱ መዳናችንን ካመን ግን፣ ያዳነን እሱ አምላክ መኾኑን ማወቅና ማመን አለብን፤ ፍጡር ፍጡራንን ማዳን አይችልምና:: ራሱ መዳን የሚያስፈልገው ስለሆነ ለምሳሌ ይላል አትናቴዎስ ለጉባኤው ባሰማው መልስ፣ በማቴዎስ ወንጌል የተማርነው የጠፋው በግ ምሳሌ መሳውን የሰው ዘር የሚመለከት ነው፤ ፈላጊውም ቃል የእግዚአብሔር ልጅ ነው:: «ቃል» ፍጡር ከተባለ የጠፋው ርሱው ራሱ ነዋ! ብሎ አትናቴዎስ ለጉባኤው ሲያሰማ ኦርቶዶክሳውያኑ በደስታ ተዋጡ:: አርዮስና መሰሎቹ ግን አመድ ለበሱ::

በጉባኤው ከቀረቡት የአርዮስ ሐሳቦች በጣም የሚያስቀው በገድል በትሩፋት ስለ ከበረ፣ አምላክ ተብሎ ሊሰገድለት ይገባል የሚለው ነበር:: መልስ ሰጪዎቹ እነ አትናቴዎስ ለዚህ ሲመልሱ ክርስቶስ ከባሕርይ አባቱ ከአብ ጋር አንድ ነው:: ይህ ካልሆነ ግን ማለት ፍጡር ነው፣ ካልን ለሱ የእምልኮት ስግደት ማቅረብ አምልኮ ባዕድ (አምልኮ ጣዖት) ነው ሲሉ ሐሳቡን ተቃውመዋል:: ክርስቶስ በመዋዕለ ሥጋዌው፣ በሥጋ ርስት በሥጋዌ ሥርዓት ሐዋርያት ደቂቀ አዳምን አኀውየ (ወንድሞቼ) ማለትን አያፍርም፤ ወልደ እግዚአብሔር ወልደ አዳም ኾኗልና:: (ዕብራ 2÷11) የአብ የባሕርይ ልጅነቱን በተናገረበት አንቀጽ ግን፣ ራሱን ከጻድቃን ከሰማዕታት ጋር ቆጥሮ አልተናገረም፣ «አቡየ» አባቴ «አቡክሙ» አባታችሁ አለ እንጂ፣ «አቡነ» አባታችን አላለም:: አብም ተቀዳሚ ተከታይ የሌለው ለአንድ ልጁ፣ አባትነቱን በመሰከረበት አንቀጽ፣ በዮርዳኖስ ከዮሐንስ ጋር አዳብሎ አቀናጅቶ ወይም በደብረ ታቦር ከዮሐንስ ከያዕቆብና ከጴጥሮስ ጋር አዳብሎ «ውሉድየ» ልጆቼ አላለም፤ አጥርቶ ለይቶ «ወልድየ» ልጄ አለው እንጂ::

ከዚህ ሁሉ ክርክርና መልስ በኋላ፣ በጉባኤው ከነበሩት አባቶች ብዙዎቹ የቤተ ክርስቲያንን የእምነት አውታር የሚያናውጥ ይህ የአርዮስ አሳብ ሰው ሰራሽ አስተሳሰብ እንጂ፣ ከእግዚአብሔር አምላካዊ ምሥጢር ጋር የማይዛመድ መሆኑን ሲገልጡ የሚከተለውን አሳብ ሰጥተዋል:: ክርስቶስ ራሱም ሆነ ሐዋርያት ያስተማሩን በልብ የሚኖር እምነትና እውነት እንጂ፣ በሳይንቲፊክ፣ በምርምርና በፍልስፍና የሚታወቅ አፍአዊ ዕውቀት አላስተማሩንም፣ ሲሉ ሃይማኖት የፍልስፍና ተገዥ አለመሆኑን በአጭር አገላለጥ ተናግረዋል:: በጉባኤው ላይ አውሳብዮስ ዘቂሣርያና አውሳብዮ ዘኒቆሚዲያ አርዮስን ለመደገፍ፣ «ወልድ አብን ይመስለዋል» የሚል አሳብ አቅርበው ነበር:: ነገር ግን ጉባኤው ይህ ከአርዮስ አመለካከት ልዩ ሆኖ ስላላገኘው አልተቀበለውም::

በመጨረሻም ጉባኤውም ስለ ወልድ አምላክነትና በባሕርይም ከአብ ጋር አንድ ስለመሆኑ፣ አትናቴዎስ ያቀረበውን የመጽሐፍ ቅዱስ መረጃ፣ አርዮስ ከሰበሰባቸው ጋር በማወዳደር ከተመለከተና ካጠና በኋላ፣ አርዮስ ወልድ ፍጡር በመለኮቱ ለማለት ያበቃው በፍልስፍና ገመድ ተጠልፎ ዐወቅሁ ተራቀቅሁ በማለት እንጂ፣ ያቀረባቸው የቅዱሳት መጻሕፍት ጥቅሶች የወልድን ፍጡርነት ስለማይናገሩ፣ ከስሕተቱ አልመለሰም ካለ፣ ትምህርቱም እሱም በሐዋርዊት ቤተ ክርስቲያን ቦታ የላቸውም፤ ሲሉ ለቤተ ክርስቲያን በተሰጣት ሥልጣንና መብት አውግዘው ለይተውታል፤ ወደ እስክንድርያም እንዳይሔድ ወስነውበታል::

እሱን ካወገዙ በኋላ፣ የቤተ ክርስቲያንን እምነት ከፍልስፍና ለይተው መጽሐፍ ቅዱስ «ቃል» የሚለውና «ወልድ» የሚለው አንድ መሆኑን አብራርተው፣ የወልድንም መገኘት አትናቴዎስ እንዳቀረበው «ዘእምባሕርየ አብ» ወይም «ዋሕደ ባሕርይ ምስለ አብ» በማለት የመለኮትን አንድነት፣ የአካላትን ሦስትነት፣ የወልድን አምላክነት በመጽሐፍ ቅዱሳዊ አንቀጸ ሃይማኖት አጽድቀዋል:: አሁን በቤተ ክርስቲያን የሚሠራበት የሃይማኖታችን ቀኖና ይኸው ነው:: እሱም አሥራ ሁለት አንቀጽ ያለው ሲኾን፣ ከነዚህ ሰባቱ በኒቅያ ጉባኤ በሠለስቱ ምዕት የተረቀቁ ናቸው:: ሌሎቹ አምስቱ ግን በሁለተኛው ጉባኤ በቁስጥንጥንያ ሊቃውንት የቀረቡ ናቸው:: አሁን የሠለስቱ ምእትን አንቀጸ ሃይማኖት እንደሚከተለው እናቀርባለን::

***የኒቂያ አንቀጸ ሃይማኖት***

1. ነአምን በአሐዱ አምላክ አብ አኃዜ ኵሉ ገባሬ ኵሉ ዘያስተርኢ ወዘኢያስተርኢ (በአንድ አምላክ እናምናለን ሁሉን የያዘ አባት ሁሉን የፈጠረ የሚታየውንም የማይታየውንም)::

2. ወበአሐዱ ኢየሱስ ክርስቶስ ወልደ እግዚአብሔር ባሕቲቱ፣ ዘተወልደ እምአብ ወውእቱ (ዘኒ) እምባሕርየ አብ አምላክ እምአምላክ፣ ብርሃን ዘእምብርሃን፣ አምላክ ዘበአማን፣ እምአምላክ ዘበአማን፣ ዘተወልደ ወአኮ፣ ዘተገብረ፣ ዘዋሕድ (ዘእሩይ) ምስለ አብ በመለኮቱ፣ ዘቦቱ ኩሉ ኮነ ተፈጥረ ዘበሰማይኒ ወዘበምድርኒ (በእግዚአብሔር ልጅ በአንድ በኢየሱስ ክርስቶስም እናምናለን፤ ብቻውን ከአብ የተወለደ፣ ይኸውም ከአባቱ ባሕርይ፣ ከአምላክ የተወለደ (የተገኘ የተወለደ) አምላክ፣ ከብርሃን የተወለደ (የተገኘ)፣ እውነተኛ አምላክ፣ የተወለደ እንጂ ያልተፈጠረ በመለኮት ከአባቱ ጋር አንድ የሚሆን ሁሉ በሱ የሆነ (የተፈጠረ) በሰማይም በምድርም)፣
3. ዘበእንቲአነ ለሰብእ ወበእንተ መድኃኒትነ ወረደ ተሰገወ ወተሰብአ (ስለኛ ስለ ሰዎች ስለ መዳናችንም (መድኃኒታችንም) የወረደ ሥጋ የሆነ ሰውም የሆነ)::
4. ሐመ ወሞተ ወተቀብረ (የታመመ (መከራ የተቀበለ) የሞተና የተቀበረ)::
5. ወተንሥአ ዳግመ በሣልስት ዕለት (በሦስተኛውም ቀን ዳግመኛ የተነሣ)::
6. ዐርገ ውስተ ሰማያት (ወደ ሰማያት የወጣ፣ ያረገ)::
7. ወይመጽእ ይኰንን ሕያዋነ ወሙታነ፤ ወበመንፈስ ቅዱስ (ሕያዋንና ሙታንን ይገዛ ዘንድ ዳግመኛ የሚመጣ::)

በመንፈስ ቅዱስም እናምናለን:: (ይህ የመጨረሻው አንቀጽ በኒቅያ ጉባኤ ተጀምሮ በቊስጥንጥንያ ጉባኤ ስለ ተፈጸመ፣ ከኹለቱም ይነሣል፤ የሚቆጠረው ግን ከቊስጥንጥንያው ነው::) ሠለስቱ ምእት ይህን አንቀጸ ሃይማኖት ለቤተ ክርስቲያን ባስረከቡበት ሰዓት የሚከተለውን የማስጠንቀቂያ ውግዘት አስተላልፈዋል:: ከዚህ ኦርቶዶክሳዊ የሃይማኖት ቀኖና አልፈው አንዱን አካል ወልድን ከአብ ለይተው፣ ያልነበረበት ጊዜ ነበረ የሚሉ ወይም ከመወለዱ በፊት አልነበረም የሚሉ፣ ከኢምንት ወይም እምኀበ አልቦ ተፈጠረ የሚሉ፣ ፍጡር ነው የሚሉ ወይም በባሕርዩ መለወጥ አለበት የሚሉትን እነዚህ ሁሉ፣ በሁሉ ያለች ሐዋርያዊት ቤተ ክርስቲያን ዘእግዚአብሔር ታወግዛቸዋለች፤ ሲሉ ውሳኔያቸውን በውግዘት ዘግተዋል::

በቤተ ክርስቲያን አነጋገር፣ ትምህርተ ሃይማኖት (ዶግማ) በጉባኤ ተወሰነ ሲባል፣ ሰዎች ተሰብስበው ይህን ማመን አለብን ብለው በድምጽ ብልጫ ተስማምተው የጋራ መግለጫ አወጡ ማለት አይደለም:: ገበሬ በእህሉ አጠገብ ወይም እህሉን መስሎ አዝመራውን የሚጎዳ አረም ሲበቅል፣ ከእህሉ መካከል ነቅሎ እንዲጥል፣ ቤተ ክርስቲያንም በዓይኗ አይታ በጆሮዋ ሰምታ በእጇዋ ዳስሳ በምታውቀውና በምታምነው እውነት አጠገብ፣ የራሷን እውነት መስሎ ራሷን የሚጎዳ የመናፍቃንን የአስተሳሰብ አረም ነቅላ ለመጣል ጉባኤ ታደርጋለች:: አረሙን ነቅላ ጥላ፣ ትምህርት አዝመራዋን ትከላከላለች:: ለምሳሌ የወልድን አምላክነት የደነገጉትና የወሰኑት በ325 ዓ.ም የተሰበሰቡ አበው አልነበሩም፤ የወልድ አምላክነት በቅዱሳት መጻሕፍት ምስክርነትና ራሱም ጌታ በሠራቸው ሥራዎች የታወቀ የተረዳ ነው:: ቤተ ክርስቲያንም ከሐዋርያት ዘመን ጀምራ ክርስቶስ «ወልደ እግዚአብሔር» መሆኑን እየመሰከረች እስከ አርዮስ መነሣት ደርሳለች አርዮስ በተነሣ ጊዜ በ325 በኒቂያ የተደረገው ጉባኤ የሰጠው ውሳኔም፣ የሐዋርያት ትምህርት ከአርዮስ አሳብ ጋር እንዳይጣለፍ ለይቶ ለማሳወቅ ነው::

ይህን ያልንበት ዋናው ምክንያት ብዙ ምዕራባውን፣ ይልቁንም የፕሮቴስታንት (ፀረ ማርያም) እምነት ተከታዮች፣ ትምህርተ ሃይማኖት (ዶግማ) በየጊዜው በድምጽ ብልጫ የሚወሰን የሰው ሐሳብ ነው እያሉ ባፍም በመጣፍም ስለሚናገሩ፣ እውነቱን እንዲያውቁት ለማስረዳት ያህል ነው:: ይህ የመጀመሪያው ጉባኤ እንዲሰበሰብ ዋና ምክንያት የሆነው የአርዮስ ጉዳይ ቢሆንም፣ ሠለስቱ ምእት እግረ መንገዳቸውን ቤተ ክርስቲያን በውጭና በውስጥ ስላላት ያስተዳደር ሥርዓት፣ ስለ በዓላትና አጽዋማት፣ ስለ ኤጲስ ቆጶሳት መብትና ሥልጣን፣ ስለ ሀገረ ስብከት ክልል ውሳኔ አስተላልፈዋል::

ባጠቃላይ ማለት ሥርዓትንና ሃይማኖትን በሚመለከት ጉዳይ ላይ፣ በጉባኤ ኒቂያ ኻያ ቀኖናዎች ተወስነዋል:: (ኋላ ግን በየጊዜው በሠለስቱ ምእት ስም ሌሎች 84 ቀኖናዎች ተቀላቅለውባቸዋል::) እነዚህ ኻያ ቀኖናዎች የቤተ ክርስቲንን የውስጥ ሥርዓት የሚመለከቱ ናቸው:: ለምሳሌ ስለ ፋሲካ በዓል ክርስቲያኖች ፋሲካቸውን ከአይሁድ ፋሲካ ጋር እንዳያከብሩ፣ ትንሣኤ ምን ጊዜም እሑድ ቀን እንዲውል ከመጋቢት 14 ቀን በኋላ እንዲውል፣ ይኸውም የሚያዝያ ጨረቃ ሠርቅ ካደረገች በኋላ ማለት ነው:: በጥቢ ወራት እንዲሆን፣ (በኛ በበጋ) ዕሪና መዐልትና ዕሪና ሌሊት በሚተካከልበት ከዚህም ሁሉ ጋር በቤተ ክረስቲያን ውስጥ ከሀገረ ስብከት መገንጠልን የጀመረ የመስጢዮስን ድርጊት አውግዘዋል:: (ይህ ሰው በእስክንድርያ መንበር ሥር ይተዳደር የነበረ፣ የአስዮጥ ኤጲስ ቆጶስ ነበር፤ ከተፍጻሜተ ሰማዕት ጴጥሮስ ጋር አለመግባባትን ፈጥሮ በመጨረሻም ሃገረ ስብከቱን ከእስክንድርያ መንበር ገንጥሏል:: እነ አርዮስንም ያሸፈተ እሱ ነው ይባላል:: በዚህ ምክንያት ተፍጻሜተ ሰማዕት ጴጥሮስም አውግዞታል::) ይህን በማስመልከት በአሕዛብ አገር የምትገኝ ቤተ ክርስቲያን ሁሉ፣ ክርስትናን ለተቀበለችበት ሐዋርያዊ መንበር አካል ናት፤ ልትለይ አይገባም ሲሉ፣ የቤተ ክርስቲያንን አንድነት የሚያጸና ቀኖና ወስነዋል:: (ግብጻውያን ኢትዮጵያዊ ጳጳስ እንዳይሾም የሚል ተቀጽላ ሕግ የጨመሩት አሁን ባየነው ሕግ ላይ ነው::)

ሃይማኖትን አጽንተው አርዮስን አውግዘው ወደመጡበት ሊመለሱ ሲሉ፣ ቆስጠንጠንጢኖስ ተቀብሎ የመሰነባበቻ ንግግር አድርጎላቸዋል:: «አባቶች ሆይ፣ እንደ መልካም ባለ መድኃኒት ኹኑ፤ ባለ መድኃኒቶች የበሽታውን ዓይነት ከነመድኃኒቱ ለይተው ያውቁታል፤ ስለዚህ ለሁሉ በሁሉ ይገኙለታል:: አሁንም በሰላም አገራችሁ ግቡ፤ ለኔም ከልብ ጸልዩልኝ» ብሎ የመሰነባበቻ ንግግር አደረገላቸው:: እነሱም ጉባኤው በተጀመረ ጊዜ ሰጥቷቸው የነበረውን ሰይፍ መልሰው አስታጠቁት ዘውዱን ደፉለት፤ ቀለበቱን አገቡለት:: ያረቀቁትንና ያጸደቁትን አንቀጸ ሃይማኖትም አስረከቡት:: በይፋ ልትመሰክረውና ልትጠብቀው ይገባሃል ሲሉ:: ሠለስቱ ምእት ያረቀቁትን አንቀጸ ሃይማኖት ከሊብያ የመጡ ሁለት ኤጲስ ቆጶሳት ቴዎናስ እና ሴኩንዳ ስለተቃወሙ ከአርዮስ ጋር አብረው ተወግዘዋል::